በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ***ክርስትና - የሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ትክክለኛ ምርጫ***

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**የካቲት ፩ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# ክርስትና - የሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ትክክለኛ ምርጫ

"እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።" ***ኢያሱ 24፡1-33፡፡*** እንዳለ ምርጫችን እግዚአብሔር፣ ወዳጆቹ ቅዱሳን፣ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት፣ የቀናው ትውፊታችንና ሥርዓታችን ነው፡፡ ኤር 6፡16፣

## *በሰለጠነው ዓለም የሚገጥሙን ፈተናዎች*

1. በሃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሱ ሐሰተኞች መበራከት "ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።" ***ቀዳ ዮሐ 4፡1፡፡***
2. አክራሪነት
3. ያለ ቅድስና መኖር መስፋፋቱ፡- ሲጋራ፣ አልኮል መጠጦችን፣ አደንዛዥ እጾችን መጠቀምና ግብረ ሰዶማዊነት:: "ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" ***ቀዳ ቆሮ 6፡20፡፡***
4. በቁሳዊ አስተሳሰብ መመራትና ዋጋ ወይም ትርጉም በሌላቸው ነገሮች መደሰት እየደገ መሄዱ
5. በርካታ ቤተሰብ በተለያየ ምክንያት (ስደት፣ የሥራ እጦት፣ መገለል፣ አድልዎ፣…)መበተኑ
6. የፍቺ ቁጥር በየጊዜው እያደገ መሄድ
7. ሃይማኖታዊ አኗኗር ጊዜ ያለፈበት ሆኖ እየተቆጠረ መምጣቱ፡፡"በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ።" ***ሮሜ 2፡24፡፡***

## *በነዚህ ሂደቶች እርካታ አግኝተናል?*

- ከእግዚአብሔር ተለይታ በምትጓዘው ዓለም ውስጥ ስንኖር ደስታ አለን?
- እግዚአብሔርስ ደስ ያሰኘን ዘንድ ዕድል ሰጥተነዋል?
- በግል በያዝነው ፍላጎታችን ላይ ለመደራደር ፈቃደኞች ነን?
- የግል ፍላጎታችንስ ወደ ቅድስና ለመድረስ ከያዝነው ግብ እየገደበን አይደለምን?
- ሁሉን ነገር ከመንፈሳዊ ዓላማችን  አንጻር ትኩረት ሰጥተን እንመረምራለን ?
- ታዲያ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

# *ክርስትና - የሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ትክክለኛ ምርጫ*

***ምን እናድርግ?***

1. "ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም። ።" ***ቀዳ ቆሮ 10፡23፡፡***

2.በሁሉ ዘንድ የክርስትናውን ሕግ ማዕከል የሆነውን ፍቅርን በመያዝ እንኑር፡፡ ***ቀዳ ቆሮ 13፡1-13፡፡***

3.ምሕረትና ይቅርታን እንዲሁም የእግዚአብሔርን ረዳትነት ልናገኝ በምንችልበት ጎዳና ውስጥ እንገኝ፡፡

4.በቤተ ክርስቲያን ለምናገኛቸው ለወንድሞቻችንና ለእህቶቻችን ለውድቀታቸው ምክንያት ከመሆን እንቆጠብ፡፡ ***ሉቃ 17፡2፡፡***

4. "ሥጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው።" ***ሮሜ 14፡21*** **እንደተባልን ራሳችንን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በመመልከት የምንከባከብና ለጥፋታቸውም ምክንያት ከመሆን እንጠንቀቅ፡፡**

5. "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።" ***ቀዳ ቆሮ 3፡16-17፡፡*** **እንደተባልን ዘወትር በቅድስና እንኑር፡፡**

# ክርስትና - የሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ትክክለኛ ምርጫ

## በዚህ ክፍለ ዘመን በትክክለኛ መርጫ ስንኖር ሌላ ምን እናድርግ?

1. ኃላፊነት የሚሰማን መሆን (ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከቤተ ክርስቲያን ትውፊት፣ ከመምህራን፣ ከነፍስ አባቶቻችን በተማርነው መሠረት በውሳኔአችን፣ በሥራችን፣ በድርጊታችን ሁሉ ተጠያቂነታችንን በመቀበል እንመላለስ)
2. ጊዜያዊ ደስታ ወይም ጥቅም ላይ ተመሥርተን የምንሠራውን ሁሉ መርምረን እንተው
3. የሚደረግብንን ሁሉ በደስታ በመቀበል በምትኩ ይቅር እንበል
4. ሁሉን በሕይወታችን በሚያከናውነው በአምላካችን በመድኃኔዓለም አማካይነት የሕይወታችንን መርሕና ዓላማ እንወስን፡፡
5. እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ እንዳለ እናስተውል፡፡
6. የምንሠራውን ሁሉ ለምን እሠራዋለሁ? በሥራውስ እግዚአብሔር ይከብራል? ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያኔስ ትጠቀምበታለች? በምሰራውስ ሥራ መድኃኔዓለምን እገናኘዋለሁ ወይስ እለይበታለሁ በማለት ሥራችንን ሁሉ ዘወትር እንመርምር፡፡

"ብሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን?" *ካል ቆሮ 13፡5፡፡* እንዳለን፡፡

# <u>*ክርስትና - የሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ትክክለኛ ምርጫ*</u>

## <u>*ምንን እናስወግድ?*</u>

"ስለዚህ ምክንያት የአይሁድን ተረትና ከእውነት ፈቀቅ የሚሉትን ሰዎች ትእዛዝ ሳያዳምጡ፥ በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ ውቀሳቸው። " <u>*ቲቶ 1፡14፡፡*</u> እንደተባልነው የሚከተሉትን ከእኛ እናርቃቸው፡፡

1. **የማንቆጣጠረውን ስሜት፡፡** <u>*ገላ 5፡19፡፡*</u>
2. **ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እየኖርንና እያሰብን አለን የምንለውን ራዕይ፡፡**
   ‹‹ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋዋለት ናችሁና። » <u>*ያዕ 4፡14፡፡*</u>
3. **በእግዚአብሔር ጸጋ (ስጦታ) ያልታገዘ *ሥራችንን* (አገልግሎታችንን)፡፡** *ያዕ 1፡17*
4. **ምድራዊውን ከሰማያዊው በላይ ማድረግን፡፡** ‹‹ሰው በከንቱ ወራቱ ቍጥርና እንደ ጥላ በሚያሳልፈው ዘመኑ በሕይወቱ ሳለ ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅ ማነው? ወይስ ለሰው ከፀሐይ በታች ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን ማን ይነግረዋል? » <u>*መክ 6፡12፡፡*</u>
5. **ራስ ወዳድነት፣ ምግባረ ብልሹነት የሰለጠነበትን አካሄድ ማገዝን፡፡** ‹‹ስለዚህ እናንተ አእምሮ ያላችሁ ሰዎች፥ ስሙኝ ክፋትን ያደርግ ዘንድ ከእግዚአብሔር፥ በደልንም ይሠራ ዘንድ ሁሉን ከሚችል አምላክ ይራቅ።››
   <u>*ኢዮ 34፡10፡፡*</u>
6. **እምነትና ፍቅር አልባ መሆንን፡፡** <u>*ዕብ 11፡6፣ ቀዳ ቆሮ 13፡1፡፡*</u>
7. **የክርስቶስ አካል ከሆነች ከቤተ ክርስቲያን መለየትን፡፡** <u>*ኤፌ 1፡21-23፡፡*</u>

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org